# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 153 ሚያዝያ 13 2003 ገጽ 1


**የአባይ ግድብ ሃሳብ የቻይናና ህንድ ቱጃሮችን ለመርዳት የወጣ እቅድ ነው። "የህዳሴ ግድብ" ባዶ ተረት ቢሆንም ለዚህ ተብሎ ከሚጠራቀመው ገንዘብ ተቆንጥሮ ለቻይናና ህንድ ልማት ሊውሉ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ለም መሬቶችን ለቻይናና ህንድ ከተሸጡ ወዲህ መንገዱም፣ መብራቱም መስኖውም የሚገባው ለእነሱ መሆኑ ልብ ይሏል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ፍሪደም ሃውስ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢንተርነት ነጻነትን በመገደብ ከሳራ በታች ካሉት አገሮች ብቸኛ እንደሆነ አጋለጠ

ተቀማጭነቱ በአሜሪካን አገር በዋሽንግተን ዲስ የሆነው እና በዲሞክራሲ፤ በፖለቲካ ነጻነትና የሰብዓዊ መብትቶች ዙሪያ ላይ በአለም አቀፍ ደረጃ ምርምር የሚያደርግ ፍሪደም ሃውስ በመባል የሚታወቅ ተቋም የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መሰረታዊ የሆነ በኢንተርነት መረጃ የማግኘት ነጻነትን ይገድባል ሲል ሰሞኑን ባወጣው አመታዊ ሪፖርት ከሰሰ።

እንደፊሪደም ሃውስ ሪፖርት 85 ሚሊዮን የሚገመት ህዝብ በሚኖርባት አገራችን የኢንተርነት ስርጭት ከዜሮ ነጥብ አምስት በታች ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ከቁጥር በማይገባ ስርጭ ላይ አገዛዙ የኢንተርነት ግንኙነቶችን ሳንሱር በማድረግ እና የፖለቲካ ክርክሮች፤ ውይይቶች ወይም አስተያየቶች የሚካሄዱባቸውን ድህረ ገጾች ጨርሶኑ በአገር ውስጥ እንዳይታዩ የመዝጋት የአፈና እርምጃ ይወስዳል።

በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒከሽን አገልግሎት እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላት ቻይና፤ አገዛዙ ኢንተርኔትንና የሳታላይት ሞገዶችን ለመጥለፍ በሚያካሂደው ዘመቻ ዘመናዊ መሳሪያዎችን በማቀበል ብቸኛዋ ተባባሪ አገር እንደሆነች ሪፖርቱ አክሎ አጋልጦአል። የአለም አቀፍ ቴሌኮሚኒኬሽን ድርጅት ባለፈው አመት ባካሄደው አለም አቀፍ ጥናት በኢትይጵያ ውስጥ ለኢንተርነት አገልግሎት የሚከፈለው ዋጋ ከዜጎች ወርሃዊ ገቢ ጋር ሲነፃጸር በአለም እጅግ ውድ ከሚባሉት ተርታ ይገኛል ያለው የፍሪደም ሃውስ ሪፖርት የዋጋውን ንረት በንፅጽር ለማሳየት ከፍተኛ የመረጋጋት ችግር ካለባቸው የመካከለኛው አፍሪካ አገሮች ተርታ እንደሚገኝ ገልጾ መንግሥት አልባ የሆነቺው ሱማሌ፤ ጎሬቤት አገር ጁቡቲ ፤ ኬንያና ሱዳን ከአገራችን በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ከዘገባው መረዳት ተችሎአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አዜብ መስፍን በኦሮሚያ ክልል የሚካሄደውን ሙስና ከኦህዴድ ጀርባ ሆና በበላይነት ስትመራ እንደነበር ተጋለጠ

የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ ቁንጮ ባለቤት የሆነቺው አዜብ መስፍን ከኦህዴድና ከሌሎች መሰል ባለሥልጣናት ጀርባ ሆና በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞች የተንሰራፋውን ከፍተኛ የመሬት ችብቸባ ሙስና በበላይነት ስትመረ እንደነበር የኢትዮጵያ ሳተላይ ት ቴሌቪዥን ኢሳት የኦሮሚያ ምንጮቹን በመጥቀስ ዘገበ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሙስና እናት እየተባለች የምትጠራው የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ባለቤት አዜብ መስፍን በአዲስ አበባ ዙሪያና በኦሮሚያ ክልል ሲካሄድ ከነበረው የመሬት ሽያጩ የዝሆን ድርሻውን ወደ ግል ኪሷና መኖሪያ ቤቷ መግባቱን የገለጹት ምንጮቹ ከዝሆን ድርሻ የቀረውን ትርፍራፊ ደግሞ የተወሰኑ የኦህዴድና የኦሮሚያ ባለሥልጣናትም የየድርሻቸውን አግኝተዋል በማለት ኢሳት ገልጹዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አባዱላ ገመዳ ባለአራት ፎቅ ቤቱን ተነጠቀ

አገራችንን በማፍረስ ተልዕኮ እና በሃብት ምዝበራው ወንጀል የተጠመደው ዘረኛው እና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች በትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች እና መደለያ በዙሪያው ያሰባሰባቸውን አንዳንድ ግለሰቦች በተለያየ ውንጀላ የማስወገድ ተግባሩን እየገፋበት እንደሆነ በዚህም ምክንያት አባዱላ ገመዳ የወቅቱ ተረኛ እንደሆነ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ።

ለረጅም ጊዜ የኦሮሚያ ክልልና የኦህዴድ ፕሬዝዳንት በመሆን በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን የአጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሲያስተገብር የቆየው አባ ዱላ ገመዳ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከመለስ ዜናዊ ጋር በገባበት አለመግባባት ግልጽና ስውር ተጽዕኖዎች እየደረሰበት እንደሚገኝ ለግለሰቡ ቅርበት ያላቸው ምንጮች አረጋግጠዋል።

እንደ የኦሮሚያ አካባቢ ምንጮች መረጃ በአባዱላና በመለስ ዜናዊ መካከል የነበረውን አለመግባባት የተባባሰው ሸክ አላሙዲን በኦሮሚያ ክልሉ በስሙ ይዞት የነበረውን ሰፊ የልማት ቦታ ለረጅም ጊዜ ምንም የግንባታ ሥራ አልሰራበትም በማለት እንዲወረስ ካስደረገና በአህዲድ ሥር የሚተዳደረው የድንሾ ንግድ ድርጅት በጫት ንግድ ገቢያ የነበረውን ድርሻ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ለመቆጣጠር ጣልቃ ስትገባ ለማስቆም ከተፍጨረጨረ ቦኋላ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመለስ ዜናዊ በቀጥታ የሚተላለፈው ቀጭን ትዕዛዝ ክልላችንን ይጎዳል በማለት ቅሬታ ያሰሙ ከከፍተኛ አስከ ተራ የአህዲድ አባላት ያሉ ግለሰቦች በሙስናና በኦነግ አባልነት ተወንጅለው ከርቼሌ እንደወረዱ በተለያየ ሚዲያ መዘገቡ ይታወሳል ። አባዱላ ገመዳ በትርፍነት ከተመራው የከተማ ቦታ አንዱን በቅርቡ ለድርጅቱ አህዲድ አውርሶ እንደነበረ የሚያስታውሱ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በ3 የመንግስት መ/ቤቶች ዉስጥ መመሪያን ያልተከተለ የሂሳብ አያያዝ እንዳለ የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ገለፀ

ደንብና መመሪያን ያልተከተለ የሂሳብ አያያዝ ችግር በዋነኛነት ከታየባቸዉ መ/ቤቶች መካከል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ዘርፍ፡ የመከላከያ ሚኒስቴርና የኢምግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች ዋና መመሪያ እንደሆኑ የዋናው ኦዲተር ቢሮ አስታወቀ።

የፌዴራል ዋናዉ ኦዲተር ይህን የገለፀዉ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለመንግስት ወጪ አስተዳዳርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ነው።

በዚህም መሠረት፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ዘርፍ 21,736,349.98 ብር ገቢ ሂሳብ፣ 6,630,327.06 ብር ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ወጪ ሂሳብ፣ እንዲሁም በመከላከያ ሚኒስቴርና በኢምግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ በድምሩ 2.8 ሚሊዮን ተከፋይ እና 5.3 ሚሊዮን ተሰብሳቢ ሂሳብ እንደሚታይ ተገልጿል። የመ/ቤቶቹ የሂሳብ አያያዝ ግልፅነት የጎደለዉ በመሆኑ ትክከለኛነቱን ለማረጋገጥ እንደማይቻል በሪፖርቱ ላይ ተጠቅሷል። በሪፖርቱ ላይ የተጠቀሱት ሶስት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለገዢዉ ወያኔ ፓርቲ የፖለቲካ አፈፃፀም እጅግ የቀረቡ መሆናቸዉ አሰፈፃሚነታቸዉ በማንአለብኝነት ለህገ ወጥ የሂሳብ አያያዝና የበጀት አጠቃቀም እንደዳረጋቸው ይታወቃል።

## ኢትዮጵያዊያን በለንደንና ጀርመን ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፍ አካሄዱ

ወያኔ ወደ ለንደን ሊመጣ ነው ተብሎ ወሬው ከተሰማበት ጊዜ ጀምረው በመጣበት መንገድ አሳፍረው ለመመለስ ከፍተኛ ዝግጅት ሲያደርጉ የሰነበቱት በለንደንና ጀርመን የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን የዘረኛውን አገዛዝ መልእክተኞች አሳፍረው፣ አዋርደውና አሸማቀው፣ ስብሰባው በታቀደው መልኩ እንዳይካሄድ ማድረጋቸውን ዘጋቢዎቻችን ከለንደንና ጀርመን ከላኩልን ሪፖርቶች ለማወቅ ተቿሉአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሚያዝያ 8 ቀን 2003 ዓም ወያኔ የተለመደውን የሃሰት ፕሮፖጋንዳውን በስደት ወጪ አገር ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለማሰራጨት በለንደንና ጀርመን ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ በየአዳራሾቹ ዘልቀው በገቡ ተቃዋሚዎች እና ከስብሰባው አዳራሽ መግቢያ ላይ ቁመው የተቃውሞ ድምጻቸውን ሲያሰሙ በነበሩ እጂግ በርካታ ሰልፈኞች መጨናገፉን የግንቦት 7 ዘጋቢዎች ከየሥፍራው ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዘገባ ገለጹ።

ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ የወያኔ መለከተኞችን እያሳፈሩ በመመለሳቸው የሚታወቁት በለንደን የሚገኙ እጂግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ካገር ቤት የተላኩትን የመለስ ዜናዊ ባለሟሎችን የተለያዩ መፈክሮችን በማሰማት መግቢያና መውጫ ቀዳዳ አሳጥተዋቸው እንደነበር ታውቋል፣ ፣ ሰልፈኞቹ ሲያሰሟቸው ከነበሯቸው መፈክሮች ውስጥ መለስ ነፍሰ ገዳይ ነው፣መለስ እና ጀሌዎቹ ለፍርድ ይቅረቡ !! የተጠማነው ፍትህና ዴሞክራሲን ነው፣ ነጻነታችንን ዛሬዉኑ እንፈልጋለን፣ መለስ ዛሬውኑ ከስልጣን ይውረድ፣ የሚሉ እንደሚገኙበት ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የትግራይ ገዢ ጉጂሌ በተለይም በሰሜን አፍሪቃ ሃገራት ውስጥ ህዝባዊ አመጾች በመፋፋማቸውና ለራሱም እንደማይቀርለት በመረዳቱ የተለያዩ አጀንዳዎችን ለኢትዮጵያዊያን በመስጠት እንደለመደው በህዝብ ትከሻ ላይ ተፈናጥጦ የመቆየት መፈራገጥ እያደረገ መሆኑን በርካታ የዜና አውታሮች ሲዘግቡት እንደቆዩ አይዘነጋም፣ ፣ አንዴ ከኤርትራ ጋር በሌላ በኩል ደግሞ ከግብጽ ጋር ጦርነት ልገጥም እቺላለሁ በማለት የህዝብን ስሜት ለማደብዘዝ ቆርጦ የተነሳው ወያኔ፣ እቅዱ አልሳካለት ሲል፣ አሁን ደግሞ አባይን እገድባለሁ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ ከኔ በላይ ለልማት ተቆርቋሪ ላሳር ነው በማለት የማወናበድ ዘመቻውን በሰሜን አሜሪካ ሃገራትም ሙከራ አድርጎ ከፍተኛ ኪሳራ የደረሰበት መሆኑም ታውቋል።

## ህዝብ ሲያስመርር የነበረው የሐረሪ ክልል የመሬት አስተዳደር ሹም ተገደለ

የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ የጭቆናና አፈና አገዛዝ ያንገሸገሻቸው ኢትዮጵያዊያን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ላይ ጠንከር ያለ ርምጃን መውሰድ መጀመራቸው የሚታወቅ ሲሆን ሰሞኑን የሐረሪ ክልል የመሬት አስተዳደርና የካሳ ክፍያ ኃላፊ የነበረው ሐሺም ኢድሪስ በጥይት ተደብድቦ መገደሉን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ለማወቅ ተችለአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ለወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሆድ አደር በመሆን በህዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጽም የቆየው ሃሺም ኢድሪስ የተዘፈቀበት የሙስናና አድሏዊ አሰራር እጂግ ያበሳጫቸው ግለሰቦች በርካታ መሆናቸውን ከነኝህ ውስጥ አንዱ ብስጪታቸው ከሚገባው በላይ በማለፉ ርምጃውን መውሰዳቸውን ገልጿል፣ ፣ የወያኔው ሆድ አደር ሃሺም ህይወቱ ከማለፉ በፊት ቀደም ብሎ በሃረር ከተማ ፈረስ መጋላ ተብሎ ከሚጠራው የከተማው እምብርት ላይ በጥይት ተመቶ ቆስሎ እንደነበርም ተያይዞ የደረሰን ዜና አሳይቷል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ የሚፈጽመው ግፍና በደል ልኩን አልፎ መፍሰስ ከጀመረ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህም አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች የሚገኙ ዜጎች፣ የአገዛዙ ታማኝና ሆድ አደር ባለስልጣናት እየፈጸሙ ላለው ልክ ያጣ በደል ተገቢውን ቅጣት እየሰጡ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሱለይማን አህመድ የተባሉ የሃረር ከተማ ነዋሪ በአገዛዙ ሆድ አደር ባለስልጣን ላይ የተወሰደውን የግድያ ርምጃ አስመልክቶ ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት በተለይም በሃረሪ ክልል ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአባይ ግድብ:- የመለስ ዜናዊ አዲሱ ማጭበርበሪያ

እየተብላላ ያለውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለማስቀረትና ጥቂት ተጨማሪ ቀናትም ቢሆን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲል የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የማይፈለቅለው ድንጋይ እንደማይኖር ጥርጥር የለንም። ከዚህም በተጨማሪ መለስ የሚፈነቅላቸው ድንጋዮች ለሱ ያላቸውን ጥቅም እንጂ በኢትዮጵያና በትውልድ ላይ ስለሚያመጡት መዘዝ ለአፍታም አስጨንቆት አያውቅም።

የእርዳታ እህል ሸጮ መሳሪያ ለመግዛት፤ ሰላማዊ ሰልፈኛን በአጋዚ ለማስጨፍጨፍ፤ ሠራዊትን ወደ ሶማሊያ ለማዝመት፤ አገሬውን እያፈናቀለ ለም መሬቶችን በገፍ ለባዕዳን ለመሸጥ ያላቅማማ ሥርዓት አባይን ገድቤ በልማት አንበሸብሻችኋለሁ ቢለን ከመሳቅ ያለፈ ምላሽ የለንም።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት መለስ ለዘመናት ሲያጣጥለው የቆየውን አባይን የመገደብ አጀንዳን ከመቅጽፈት መምዘዙ የተለመደ ቅጥፈት ነው። መለስ ስለአባይና ስለኢትዮጵያ ትልቅነት ማውራት መጀመሩ የተለየ ነገር የተፈጠረ የመሰላቸው ወገኖች ቢኖሩም ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግን ያው የለመድነውን ብልጣ ብልጥነት መሆኑ ቅንጣትም የሚያጠራጥር አይደለም። ጥቂት ቀደም ባሉ ዓመታት መለስ ስለ አባይ ቀርቶ ስለ አባይ ተፋሰሶች ልማት የተከራከሩ በርካታ ባለሙያዎችን አዋርዷል፤ አሳዷል። በአባይና በአባይ ተፋሰሶች ልማት ላይ በርካታ ጥናቶችን ያደረጉ ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ዛሬ በስደት ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ ስልጣኔን ለማቆየት ይረዳኛል ባለ ሰዓት የማያውቀው ብቻ ሳይሆን የሚጠላውን የፕሮጀክት ጥሬ ሃሳብ አንስቶ ያለዝርዝር ጥናትና ዝግጅት "ግንባታ ጀምሬዓለሁ" ሲል አወጀ። የህዝባችንን ብሄራዊ ስሜት በመኮርኮር አባይን መገደብ የዘመቻ ሥራ አድርጎታል።

የአባይን ግድብ የፕሮጀክት ጥሬ ሃሳብ በዝርዝር ተጠንቶ የበሰለ መስሎ የቀረበው ለምንድነው?

1. ለመለስ፣ አባይ እየመጣ ያለውን አደጋ መከላከያ ጋሻው ነው። ከላይ እንደተገለፀው እኛ የምንኝበት የዓለም ክፍል በከፍተኛ የለውጥ ማዕበል ውስጥ ነው። ይህ የለውጥ ማዕበል በአካባቢያችን የሚገኙ አምባገነኖችን ከፊሎቹን የጠራረጋቸው ሲሆን ከፊሎቹን ደግሞ ነቅንቆ በብርቱ እየወዘወዛቸው ነው። ይህ ህዝባዊ የለውጥ ማዕበል ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ አይቀሬ ነው። መለስ ይህ ማዕበል ወደ ኢትዮጵያ ደርሶ እርሱንም እንዳይጠርገው የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው። የአባይ ግድብ ሃሳብ ከእነዚህ ጥረቶች አንዱና ዋነኛው ነው።
2. የአባይ ግድብ ተጨማሪ የሃብት ምንጭ ነው። መለስ በአንድ በኩል "እያንዳንዷን ብር አጠራቅመን በራሳችን አቅም ግድብ እንሰራለን" እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የራሱን መኖሪያ ቤት ለማሰራት ሰማንያ ሚሊዮን ብር ያወጣል፤ እንዲሁም ሃቅን የሚናገሩ የሬድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶ ችን ለማፈን ቢሊዮን ብር ይረጫል። የእስከዛሬው ዘረፋው አልበቃ ብሎት አሁን ደግሞ በአባይ ሰበብ የድሃውን ምሳና ራት ለመቀማት የወጣ እቅድ ነው።
3. የአባይ ግድብ ሃሳብ የቻይናና ህንድ ቱጃሮችን ለመርዳት የወጣ እቅድ ነው። "የህዳሴ ግድብ" ባዶ ተረት ቢሆንም ለዚህ ተብሎ ከሚጠራቀመው ገንዘብ ተቆንጥሮ ለቻይናና ህንድ ልማት ሊውሉ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ለም መሬቶችን ለቻይናና ህንድ ከተሸጡ ወዲህ መንገዱም፣ መብራቱም መስኖውም የሚገባው ለእነሱ መሆኑ ልብ ይሏል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በኑሮ ውድነት፣ በፍትህ እጦት በዘረኝነት እየተሰቃየ ባለበት፤ ስደት የወጣቶቻችን ህልም በሆነበት በአሁኑ ሰዓት ከዚሁ ምስኪን ህዝብ ጉሮሮ ለመቀማት አባይን መጠቀሚያ ማድረግ እጅግ የከፋ ክህደት ነው። ለዚህን ነው ኢትዮጵያዊያን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ "በባድሜ ያልታመነ በአባይ አይታመንም" የሚሉት።

**ስንት ጊዜ እንታለላለን? አሁንስ በቃን!!! የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በቅቶናል፤ አንገሽግሾናል!!!**

**በቃ!!! ገዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

### ፍሪደም ሃውስ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢንተርነት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንግሊዝ አገር የሚገኘው የማንቼስተር ዩኒቨርሲት የትምህርት ክፍል ባለፈው የፈረንጆች አመት 2010 ባካሄደው ጥናት በአዲስ አበባ ውስጥ ብሮድ ባንድ በሚባለው የኢንቴርነት አገልግሎት አንድ ሰው የኢሜል መልዕክቱን ከፍቶ ለማዬት ከ6 ደቂቃ በላይ ጊዜ እንደሚፈጅበት ገልጾ የኢንተርኔት ፍጥነት እንዲህ እንዲዘገይ የሚደረገው ሆን ተብሎ አንደሆነ አጋልጦአል።

አገዛዙ ሊደርስባቸው በማይችልባቸው የውጪ አገሮች የሚኖሩ የዲያስፖራው ኮሚኒቲ ስለአገራቸው ፖለቲካ ጉዳይ የሚለዋወጡትን አስተያየቶች አቅጣጫ ለማሳት እና ለመንግሥታቸው እጅግ ቀናና በጎ የሆኑትን አስተያየቶች በምላሽ መልክ ለመስጠት በቋሚነት የሚሠሩ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሰዎች መመደባቸውን ፍሪደም ሃውስ መረጃ እንዳለው በ2010 አመታዊ ሪፖርቱ አክሎ ገልጾአል።

የወያኔ አገዛዝ በኢንቴርኔት አማካኝነት የሚተላለፉ ማናቸውንም አይነት ይዜት ያላቸው በድምጽ እና በቪዲዮ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ሁሉ እንደዘጋ ያጋለጠው ይህ የፍሪደም ሃውስ አመታዊ ሪፖርት ከውጪ ወደ አገር ቤት የሚተላለፉ ሬዲዮኖችን በሙሉ እንደሚያፍን ለዚሁም መለስ ዜናዊ የአሜሪካ ድምጽ የአማሪኛ አገልግሎትን ለማፈን እንደተዘጋጀ በአደባባይ የሰጠውን የራሱ ቃል በማስረጃነት አቅርቦአል።

የግንቦት 7 ድምጽ በተደጋጋሚ እንደዘገበው የወያኔ አገዛዝ ኢሳት ወደአገር ቤት የሚያስተላለፈውን የሳተላይት ቴለቪዥ ስርጭት ለማወክ ከቻይና በተገዛ ዘመናዊ የሳተላይት ሞገድ መጥለፊያ ይጠቀማል። ከትናንትና ወዲያ የወጣው የፍሪደም ሃውስ አመታዊ ሪፖርትም ያረጋገጠው ይሄንኑ ሃቅ ነው።

### አዜብ መስፍን በኦሮሚያ ክልል የሚካሄደውን ሙስና . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደ ኢሳት ዘገባ በዚህ የመሬት ሙስና ውስጥ የቡራዩ ከተማ ከንቲባ የነበረው ኤባ ደበሌ፣ ወንድሙ ጄኔራል ባጫ ደበሌና የቀድሞው የሻሸመኔ ከተማ ከንቲባ ዋና ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል፡፡

አዜብ መስፍን ከኦሮሚያ ባለስልጣናት ጀርባ ሆና በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት የተሳተፉና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ወታደሮችና ኃላፊዎችን መልሶ ለማደራጀት በሚል ሰበብና በሀሰት ሥምም ዝርዝራቸው የሌሉ ሰዎችን አቅርባ በእያንዳንዳቸው ሥም ከ200 እስከ 500 ካሬ ሜትር ቦታ በፊንፊኔ ዙሪያ በሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞች ወስዳ ለተለያዩ ባለሃብቶች በእጅ አዙር በመሸጥ በርካታ ሚሊዮን ብር በሕገ-ወጥ መንገድ ማካበቷንም ምንጮቹን በመጥቀስ ኢሳት ዘግቡአል፡፡

የሙስና እናት የሆነቺው አዜብ መስፍን ቀደም ሲል ከብሄራዊ ባንክ በትዕዛዝ የወሰደቺውን ከ70 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ የባንኩን ኃላፊዎች አጨቃጭቆ ይፋ በመውጣቱ የባንክ ዕዳ ተብላ ገንዘቡን መክፈል ጀምራ እንደነበርም ተያይዞ የደረሰው ዜና ማመልከቱን ኢሳት ዘግቡአል፡፡

### አባዱላ ገመዳ ባለአራት ፎቅ ቤቱን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ምንጮቻችን በተጨማሪ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ቦሌ ወሎ ሰፈር አካባቢ ያስገነባውን ባለ አራት ፎቅ መኖሪያ ቤቱን በሙስና ሰበብ መነጠቁን ገልጸዋል። የአባዱላ ጣጣ በዚህ ሳያበቃ ተጨማሪ ክስ በጸረሙስና ኮሚሽን በኩል ሊመሰረትበት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

አባዱላ ገመዳ በቅርቡ ለህክምና ሰበብ ወደ ጀርመን መጥቶ እንደነበርና ከመለስ ዜናዊ የሚደርስበትን ውርደት ለመሸሽ ጥገኝነት የመጠየቅ ሃሳብ እንደነበረው ነገር ግን በስደት ህይወት ውስጥ ያለውን ውጣ ውረድ የመቋቋም ፍርሃት ገብቶት ሃሳቡን እንደቀየረና በመጣበት እግሩ እንደተመለሰ ተያይዞ የደረሰን መረጃ አረጋግጦአል።

ለመለስ ዜናዊ ባላቸው ታማኝነት ብቻ ዕውቀት እና ችሎታቸው በማይመጥናቸው የስልጣን ማማ ላይ ከተፈናጠጡት የጄሌ ድርጅቶች መሪዎች መካከል ከመለስ ዜናዊ የሚደርስባቸውን ውርደት ለማስቆም የምቾት ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ብዙ አይደሉም። የቤንሻንጉል እና ጉሙዝ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው ያረጋል አይሸሹም ከሁለት አመት በፊት በስደት ካናዳ ከደረሰ ቦኋላ ወዲያው ተጸጽቶ ይቅርታ በመጠየቅ ለመለስ ዜናዊ መልሶ እጁን እንደሰጠ ይታወሳል።

### የኢትዮጵያን ወቅታዊ ፖለቲካ አስመልክቶ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ- ለነፃነትና ለዲሞክራሲ መግለጫ አወጣ

የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ በመባል የሚታወቀው ድርጅት ነፃነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ይሰፍናል! በሚል ርዕስ በቅርቡ ባወጣው መግለጫ በቱኒዚያ፡ በግብፅና በሌሎችም በመካከለኛዉ ምስራቅ እና በሰሜን አፍሪቃ በመካሄድ ላይ ያሉት የህዝብ አመጾች በተመሳሳይ ጭቆና ሥር ላሉ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የአለም ክፍሎች አርዓያነት ያለው መልዕክት መስተላለፉን ገልጿል።

በኢትዮጵያ ለሚታየዉ የለዉጥ ፍላጎት መነሳሳት እነዚሁ የሕዝብ አመጾች ምክንያት እንደሆኑና ወቅቱ የአምባገነንና የፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ ስርአቶች ተወግደዉ ዲሞክራሲያዊና የህዝቦች ሉኣላዊነት የሚሰፍንበት እንደሆነ አመልክቷል።

በኢትዮጵያ ለሚቀጣጠለዉ አመፅ መሰረታዊ ምክንያት የሚሆኑትና የሚያጎለብቱት የሚያደርጉት በአገሪቱ ዉስጥ የሚታዩት ሁኔታዎች እንደሆኑ በመግለጫዉ ተጠቅሷል። በመሆኑም ይላል መግለጫዉ "እኛ የኦሮሞና የሌሎችም ጭቁን ሕዝቦች ተማሪዎች የህዝባዊ አመፁን ለመለኮስ የመጀመሪያዎቹ ለመሆን ቁርጠኝነት እንዳለን ለአለምና ለኢትዮጵያ ህዝብ እናረጋግጣለን። በባርነት ከመኖር በነፃነት መሞትን መርጠናል የሚለዉ መግለጫ " ስቃይና ባርነቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሁኑኑ እንዲወገድና ነፃነትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ያቀጣጠልነዉን ችቦ ቀሪዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ይዞ እንደሚከተለን አምነት አለን" የሚለዉ መግለጫ ሰባት ንጥቦችን አስቀምጧል።

1. የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በስታሊናዊ ድርጅታዊ መዋቅሩም ሆነ በሚያራምዳቸዉ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች በጠባብ ጎሰኝነት ላይ የተመሰረተ፡ በአገሪቱ ዘረጋሁ የሚለዉ የፌዴራል መዋቅር ለከፋፍለህ ግዛዉ አላማዉ ካልሆነ በስተቀር ምንም ትርጉም የሌለዉ፡ የኦሮሞ፡ የኦጋዴን፡ የሲዳማ እና የሌሎችንም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች በዋና ጠላትነት ያነጣጠረ መሆኑን በመግለፅ... **ላለፉት 20 አመታት በኦሮሞ፡ በኦጋዴንና በሌሎችም ጭቆና በበዘባቸዉ አካባቢዎች የሚገኙ ህዝቦች የሚያነሱትን ጥያቄ በሃይልና በህገ ወጥ መንገድ ለማፈን የሚደረገዉ ወታደራዊ ዘመቻ በአስቸኳይ እንዲቆም**
2. መለስ ዜናዊ በስልጣን ላይ ላለፉት 20 አመታት በአፈናና በጭቆና የቆዩ ከመሆኑም በላይ አገዛዙ የህዝብን ሰብኣዊ መብት በመርገጥ፡ በማንገላታት፡ በማፈናቀል፡ በማሰቃየት፡ በማሰር፡ በመግረፍና በመግደል በአስር ሺዎች የሚቆጠሩትን በየእስር ቤቱ የህሊና እስረኛ አድርጓቸዋል። **ስለሆነም የፖለቲካ እስረኞችበአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ፡ በተለይም የሰዉ ልጅን በመግረፍና በመደብደብ ለማሰቃየት የተቋቋመዉ ማዕከላዊ የምርመራ ድርጅት በአስቸኳይ እንዲፈርስና እስከመጨረሻዉ እንዲዘጋ**
3. የመለስ ዜናዊ መንግስት የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቤአለሁ ይበል እንጂ በህዝቡ ኑሮ ላይ አንዳችም ለዉጥ እንደሌለ መንግስት በሚከተለዉ የተዛባ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት ይልቁንም በሽታ፡ ድንቁርና፡ እና ረሃብ የህዝቡ ማህበራዊ ህይወት መለያ ምልክት ሆኗል። **ስለሆነም መሰረታዊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎች ስኳር፡ ዘይት እና ዳቦ የመሳሰሉትን መንግስት በአስቸኳይ ለህዝብ እንዲያቀርብና የተሳሳቱትን የገበያና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቹን እንዲያስተካክል**
4. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ እጁን ያላስገባበት እንዳለመኖሩ በተለይም በኢኮኖሚዉ ዘርፍ ባለቤታቸዉ ወ/ሮ አዜብ መስፍን የሚቆጣጠሩት ኤፈርት በሚል የሚታወቀዉ የህወሃት የንግድ ድርጅት እንደሆነ ከህዝብ የተሰወረ አይደለም። **በመሆኑም በመለስ ዜናዊ ቤተሰብ ስም የሚገኘዉ ንብረት እንዲወረስና በቤተሰባቸዉና በቅርብ አጋሮቻቸቸዉ የተፈፀሙ የሙስና ተግባሮች እንዲመራመሩ** (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በ5 አመቱ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያልተካተተው የአባይ ግንባታ (ከዝግጅት ክፍላችን)

የአባይ ግድብ ጉዳይ መለስ ዜናዊ እንደፈለገው በሚመዘውረው ፓርላማ ውስጥ ለህዝብ ጆሮ ይፋ ከሆነበት ካለፈው ወር ጀምሮ በውጥረት ላይ ያለውን የአገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት ዘልቆ እንደዋንኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ እየናኘ ይገኛል።

የአገራችንን ለም አፈር በማጠብ ለዘመናት ለሱዳንና ግብጽ በረከት ሆኖ የኖረ አባይን የመሰለ የአገሪቷን የጉስቁልና ገጽታ ለመቀየር ትልቅ ድርሻ የሚኖረው ሃብት ለማልማት ሲታሰብ እንዴት ትኩረት አይስብ ? ሆነና ነገሩ ዜናው ከአገር ተሻግሮ ከባህር ማዶ ባለው ዲያስፖራ ዘንድም ዋና የመወያያ ርዕስ ሆኖአል። ለመሆኑ ይህ የሚላኒዬም ግድብ ግንባታ ዕቅድ በምን ያህል ምስጥር ቢጠበቅ ነው እስከዛሬ በዘርፉ እውቀትና ችሎታ ካላቸው ሙያተኞች እንስቶ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን የመንግሥት መሥሪያቤቶች ጭምር ሳያውቁት ተደብቆ ለመኖር የቻለው? በምርጫ 2002 በነቅስ ወጥቶ 99.6 በመቶ የሆነውን ድምጹን ለልማታዊው መንግሥታችን በምርጫ ለሰጠው ህዝባችን እድገት ለማምጣት ታስቦ በተዘረጋው የ5አመቱ የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥስ ይህንን የመሰለ የልማቶች ሁሉ ልማት፤ የፕሮጀክቶች ሁሉ አውራ የሆነ ባለ 80 ቢሊዮን ግድብ እንዴትስ ሳይካተት ቀረ? ወይስ ለ5 አመት በፓርላማው ውስጥ መሽገው የኖሩ የኦነግ ሃይሎች ያንን ረቂቅ አዘጋጁትና የመንግሥታችንን ገጽታ ለማበላሸት አሻጠሩ? የመሳሰሉትን ከሚጠይቁ ጀምሮ " አባይ ከመገደቡ በፊት ዘረኝነት ይገደብ!! አባይን አምባገነኖች ሊገድቡት አይችሉም!! ስለ አባይ ግንባት ከማውራት በፊት ዳቦ ለተራቡት ይድረስ!! ለምርጫ ያልታመነ ለአባይ ግንባታ አይታመንም !! ወዘተ የሚሉ የተቃውሞ መፈክሮች በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ መስተጋባት ጀምረዋል። በየመሥሪያቤቱ በግዴታ በመደረግ ላይ ባለው የድጋፍ ስብሰባ ላይ ካድሬዎች ድምጽ ማጉያ ጨብጠው "የወር ደምወዝ ከመስጠት ጀምሮ አስከ አንድ ሺ ብር በሚደርስ ገንዘብ ቦንድ ለመግዛት ዝግጁ ነን " ማለታቸውን በወያኔ ቁጥጥር ሥራ ያለው ቴሌቪዥን ጣቢያ ከሚያሳየን የድጋፍ ምስል ያውም እንኳን የወር ደመውዛቸውን ለቀው የአመት ደመወዝ ብጨመርላቸውም ደስተኛ አለመሆናቸውን በፊታቸው ገጽታ ላይ የሚነበበው ጉስቁልና ከሚያሳየን ብዙዎች የመንግሥት ሰራተኞች እና የወያኔ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ሌላ የማንንም ትኩረት አለመሳቡ ግልጽ እየሆነ መጥቶአል።

ወያኔዎች ቀደም ብለው ስለአባይ ግድብ አስበውበት ቢሆን ኖሮ በ5 አመት መሪ እቅዳቸው ውስጥ ያስቀመጡዋቸው መለስተኛ ግድቦች ላይ የተመሠረተ የሃይል አቅርቦት ዕቅድ ላይ ጊዜያቸውን ባላባከኑ ነበር ብቻ ሳይሆን ከአባይ በላይ ብሄራዊ ስሜት የሚቀሰቅስ የለምና ገና ከጅምሩ ፕሮጀክቱ መቼ እና በማን እንደተጠና፤ ፕሮጀክቱን ለመገንባት የሚያስፈልግ የሰው ሃይል፤ መሳሪያ እና ገንዘብ ለማግኘት የተደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች፤ የግንባታውን ሥራ ለመሥራት በቂ እውቀትና ልምድ ያለው የየት አገር ኩባኒያ ለጨረታ እንደቀረበና ማን በምን መስፈርት እንዳሸነፈ ወዘተ የመሳሰሉት ወሬዎች በተለመደው የፕሮፖጋንዳ ማሰራጫዎቻቸው ጆሮአቸን እስኪዶነቁር በደስኮሩብን ነበር። ስለግልገል ግቤ 2 እና 3፤ ስለተከዜ፤ ስለፍንጮሃ ፤ የመሳሰሉት ላይ ያባከኑትን አየር ጊዜ ልብ ይሏል። ለዚህ ይመስላል የአውራ አምባው አምደኛ አቤ ቶኪቾ "የአባይ ግድብ ዜና ምንጩ "ብልጩ" ነው በማለት ሰው በየቤቱ የሚያወራውን በተረባ መልክ ያቀረበው። "ብልጩ" እነመለስ ቤተመንግሥት ውስጥ የሚቅሙት አይነት ምርጥ ጫት ስም ነው አሉ።

ይህም ሆኖ ግን በዲያስፖራ ከሚኖረው ወገናችን መካከል እነመለስ ህዝቡን ለማዘናጋት "የሚላኒየም ግንባታ ያሉትን" የአባይ ግድብ ዜና ያመነና ተስፋ የሰነቀ፤ "አሁንስ ልብ ሊገዙ ሳይሆን አይቀርም" በሚለው የራሱ የዋህ ግምት እራሱን አሞኝቶ ለምስራች ነጋሪነት ወደውጪ የተሰማራውን ቡድን የስብሰባ ቀን ሲጠባበቅ የነበረ የዋህ እንዳልጠፋ በሰሜን አሜሪካው እና በአውሮፓው ስብሰባዎች ታይቶአል። እነዚህ አይነቶቹ በቁጥር ባይበዙም በመለስ ሃያ አመት ሥላጣን ቆይታ በዘረፋ ከተገኘው የአገር ሃብት ተቋዳሽ መሆናቸው የሚሰማቸው ፤ የሰሜን አፍሪካው ጸረ አምባገነን ፍልሚያ በአገር ቤት የፈጠረው መነሳሳት ያስደነገጣቸው ሰዎች ጋር ተዳምረው የስብሰባውን ቦታ ለማዳመቅ በር ላይ የአይናቸውን ቀለም እየለዩ እንዲያስገቡ ከተመደቡት የህወሃት ካድሬዎች ጋር ተጋፍተውበታል። መለስ ከወደቀ "የኛ ናት ብለው እየኮሩባት ያለው የዘረኞች ስረው መንግሥት አብራ ትናዳለችና ሚቾት ደህና ሰንቢች መምጣቱ ሊያስደነግጣቸው ይገባል። ከራስ በላይ ለአሳር ብልህ አራማጆች ምን ገዶአቸው?

ለመሆኑ ህዝባችን ምን ነክቶት ነው 99. 6 በመቶ የሆነ ድምጹን ሰጥቶ የመረጠው ሃይል "አባይን ልገድብልህና ከችጋር ላላቂቅህ ነው" ሲለው "ኤረ ወጊድልኝ መቼ አድርገሄው የሚታውቀው ነውና" በማለት ጀርባውን እያዞረ ያለው? ምክንያቱ ግልጽ ነው። በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ የማይታመንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉት። ከነዚህም ጥቂቶቹ፤

1. ጉጂለው ገና ትግል ሲጀምር የሚከተለውን እምነት እና ራ ዕይ ሰንነ ነበር ። ጥቅስ *"የትግራይ ህዝብ አጸ ዮሃንስ ከሞቱ ቦኋላ በዳግማዊ ሚኒሊኪ በሚመራው የአማራ ማዕከላዊ አገዛዝ ሥር በሃይል እንዲወድቅ ተደርጎ፤ ለከፋ ማህይምነት ፤ድህነት፤ ጉስቁልናና ስደት የተዳረገ ጭቁን ብሄር ነው፤ የህወሃት አላማም ትግራይን ከአማራ ጭቆና ነጻ በማውጣት የራሷን ሪፖብሊክ መሥርታ በሰላም መኖር እንድትችል ማድረግ ነው"* የጥቅሱ መጨረሻ |የካቲት 1968 *ለህትመት ከበቃው የህወሃት መጀመሪያው መግለጫ ላይ የተወሰደ*/ ። በማለት ትግል የጀመረ ሃይል በመሆኑ ኢትዮጵያዊ ራ ዕይና አጀንዳ የለውም። ይህ ጠባብ አላማውና አጀንዳው ኢትዮጵያን የግጦሽ ማሳ አድርጎ ከሚመለከተው እንስሳ ጋር ያመሳስለዋል።
2. በ1990 ዎቹ በምስራቅ አውሮጳ የፈነዳው የለውጥ ማዕበል በኮሚኒዚም ሥርዓት ግንባታ ሥም ተቃዋሚን በመመንጠር የአንድ ፓርቲ አገዛዝ በአገራቸው ያሰፈኑትን የደርግ አይነቶቹን አገዛዝ እያስወገደ መምጣቱ ስኔና ስኞ የተገጣጠመለት ህወሃት ልክ በትረ ሥልጣኑን እንደተቆጣጠረ ህዝባችን ለዘመናት ግንብቶት የቆየውን የብሄራዊ አንድነት ስሜት እና እሴቶቹን በመናድ "የአክሱም ሃውልት ለወላይታው ምኑ ነው ከሚለው ቲዎሪ ጀምሮ ፋሽስት ጣሊያን በ5 አመቱ ወረራ ወቅት ከፈጸመቿው በማይተናነስ ወንጀል ዜጎች የአንድነታቸውና የአርበኝነታቸው መግለጫ አድርገው የሚኮሩባትን አረንጓደ ቢጫ ቀይ ባንድራችንን "ተራ ጨርቅ" በማለት ያንቋሸሸ ሃይል ስለሆነ አባይን የመሰለ ብሄራዊ መግባባት የሚሻ ትልቅ የልማት መሠረት ለመጣል ተፈጥሮው አይፈቅድለትም ከሚል እምነት።
3. ጣሊያን በህዝባችን ላይ ለፈጸመቿው ጭፍጨፋ የደም ካሳ በስንት ድርድርና ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ብርታት በደርግ ጊዜ ጣና በለስ ላይ የገነባቿውን ትልቅ ፕሮጀከት ንብረት በመዝረፍ ወደ ትግራይ ያጓጓዘ ድርጅት ነው የትግራይ ነጻነት ግንባር በትግሪኛ አጠራሩ ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ። ከጣና በለስ ፕሮጀክት በተጨማሪ የፓዌ መስኖ ልማት ፤ ጋሚበላ ተገንብቶ የነበረው ባለብዙ መቶ ሺ ሄክታር የባሮ አኮቦ መስኖ ፕሮጄክት፤ የመካከለኛው እና የታቺኛው አዋሽ መስኖ ልማቶች፤ በዋቢ ሼቤሌ ወንዚ ላይ ጂጂጋ አካባቢ የነበረ ብዙ መቶ ሺ ሄክታር ወዘተ በወያኔ እንደጠላት አገር ሃብት የተዘመተበት ፤ ፕሮጀክቶቹ ላይ የነበሩ ትላልቅ ማሺነሪዎች ቡልዶዜሮች፤ ጊረደሮች እና ሌሎች ቢዙ ሚሊዮን ዶላር ግምት ያላቸው ንብረት በወቅቱ በአሸናፊው የህወሃት ጦር ታጅበው ወደ ትግራይ አቅጣጫ መጓጓዛቸውን እንጂ አገር ውስጥ ይኑሩ ከአገር ውጪ ወደሱዳን ተሻግረው ይቸብቸቡ የሚያቁት ስብሃት ነጋ፤ መለስ ዜናዊ፤ በረከት ስም ዖን፤ ስዩም መስፍን፤ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ የመሳሰሉ የአንድ ቡድን አባላት ብቻ ናቸው።

የአገሪቱን ዜጎች እትብታቸው ከተቀበረቺባቸው የአያት ቅም አያቶቹ መሬት ይዞታ በማፈናቀል ከ 3 ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት ነጻ ሊባል በሚችል ዋጋ ለኤሽያና ለአረብ ከበርተዎች እየቸበቸበ ያለው ይህ ጸረ አገር ሃይል በገዛ አገራቸው ዜጎችን ለባዕዳን ባርነት አሳልፎ መስጠት በመጪው ትውልድ እና በአገሪቱ መጻይ እድል ላይ ሊኖረው የሚችለው ጉዳይ አያሳስበውም። ይህንና ይህንን የመሳሰሉ በአገሪቱ ሉአላዊነትና በዜጎቿ ነጻነት ላይ ከቀን አንድ ጀምሮ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል በዚህች አጭር ትንታኔ አሳይቶ መጨረሽ አይቻለም።

እነኚህ ከላይ ለመግለጽ የተሞከሩት ወያኔ በህዝባችን እና በአገራችን ላይ የፈጸማቸው ደባዎች የተፈጸሙት ሆን ተብሎ እና ታቅዶ እንደሆነ መጠርጠር አንችልም። የወያኔ ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ከተገለጸባቸው በርካታ ማስረጃዎች እነኚህ ጥቂቶች ናቸውና። መለስ ዜናዊ በጸረ ደርግ ትግል ወቅት ከግብጽ ከፍተኛ የገንዘብና መሳሪያ ድጋፍ ያገኝ እንደነበር በዚህም ውለታ ምክንያት አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ በመጀመሪያ እንዲፈርሱ ከተደረጉት መንግሥት መስሪያቤቶች አንዱ ውሃ ልማት እንደሆነና በተለይ በራሱ በአባይ እና በተፋሰሶቹ ላይ ለአመታት የተደረጉትን የጥናት ስራዎች በወቅቱ ጠቅላይ ሚንስቴር በነበረው ታምራት ላይኔ ትዕዛዝ ከውሃ ልማት መዝገብ ቤት በወታደራዊ የጭነት መኪናዎች ተጭነው እንደወጡና የት እንደደረሱ አንደማይታወቅ የአይን አማኞች አሉ። ከአንድ ሺ በላይ ከተባረሩት እነዚያ የውሃ ልማት ሰራተኞች ውስጥ ለረጅም ጊዜ በአባይ ተፋሰስ ላይ የሰሩ መሃንዲሶች፤ ሃይዲሮሎጂስቶች፤ የመስኖ ልማት ባለሙያዎች ሲገኙ ከፊሎቹ ዛሬ በስደት አለም ይገኛሉ።ከአገር የመውጣቱ ዕድል ያልገጠማቸው ከፊሎቹ ደግሞ ከሙያው ርቀው እራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ለማስተዳደር በተለያየ የሥራ መስክ ተሰማርተው ይገኛሉ። ይህንን የመሰለ ወንጀል በአገሪቱ ላይ የፈጸሙት መለስ እና ጋሻ ጃግሬዎቹ የህዝብ ብሶት ተጠራቅሞ ከስልጣን ሊጠራርጋቸው ሲቃረብ ዘዴ ዘየዱና ከማንም የውጪ ሃይል ብድር ወይም እርዳታ ሳይገኝ አባይን የሚያክል ግዙፍ ግድብ እንገድባለንና ለ5 አመት ታገሰን ብቻ ሳይሆን ገንዘብ አዋጣ ማለትም ጀምረዋል። ከአመታዊ የአገሪቱ በጄት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ከውጪ በሚገኘው እርዳታና ብድር የሚሸፍን አገዛዝ እንዴት አድርጎ ነው 80 ቢሊዮን የሚያወጣ ግዙፍ ፕሮጄክት በራሱ የሚሰራው ? አይነጋ መስሎአት አሉ?

አባይን መገደብ መቻል ወያኔ ለማጨናበር እንደሚያወራው የኤለክትሪክ ፍጆታችንን ለመርካት ብቻ ሳይሆን በየአመቱ በረሃብ አለንጋ እንደቅጠል የሚረግፈውንም ህዝባችንን በመስኖ ልማት ለመታደግ ብሎም የአገራችንን ጉስቁልና ለመቀየር ትልቅ ትርጉም ያለው የልማት ሥራ ነው። በአገር ፍቅር ስሜት እና በአርበኝነታቸው የማይታሙት የቀደሙት መንግሥታት ሳይቀሩ ይህንን ሲያልሙ ኖረው እንዳለፉ እናውቃለን። በ19ውና 20ኛ ክፍለዘመን አገራችንን ለመቀራመት ያሰፍስፉ ከነበሩት የአውሮጳ ቅኝ ገዢዎች አገራቸውን ሲከላከሉ ለኖሩ አያት ቅድም አያቶቻችንና በነርሱ ዘመን ለነበሩት መንግሥታት ያልተቻለው አባይን የመገደብ ዕቅድ ወላጆቻቸው በጣሊያን ዘመን ለፋሽስቶች ዕንቁላል ሲያቀብሉ በኖሩ የትግራይ ተወላጆች ጸረ አገር ስሜት ምክንያት ዛሬም ብሄራዊ መግባባት በአገራችን እንዳይፈጠርና የተፈጥሮ ሃብታችን ተጠቃሚ እንዳንሆን ወንጀል እየተሰራብን ነው።

ባንዳው መለስ ዜናዊና በዙሪያው የተሸኮለኮሉት የወያኔ ቁንጮዎች ወደ አስራ አራት በሚጠጋ የሰሜን አሜሪካ እና የአውሮፓ ከተሞች ያሰማሩዋቸው የአባይ ግድብ ዕቅድ ዜና ምስራች አብሳሪዎች ተልዕኮ የከሸፈውና ለአባይ ግድብ ቦንድ ሺያጭ ዘመቻ የተደናቀፈው በለላ ምክንያት ሳይሆን ወያኔን ለማመን የማይቻል በመሆኑ ብቻ ነው። ይህንን ግዙፍ የልማት ግንባታ ስብሰባ ለማካሄድ በህዝብ ገንዘብ በተከራዩ አውቶብሶች ከያሉበት ተለቅመው የስብሰባውን አዳራሽ ለማድመቅ የተገኙ የትግራይ ወንድሞቻችንም ሆኑ ለወያኔ አጎንብሰው ባገኙት የከተማ ቦታ ከ124 ካሬ ሜትር ባልበለጠ ቦታ ላይ ለሰሩት ቤት የንበረት ባለቤትነት ያስጠበቁ መስሎአቸው ወያኔ በየአገሩ ባሉት ኤምባሲዎቹ አማካይነት ለሚያደርገው ስብሰባ የሚያጅቡ የሌሎች ብሄረሰቦች ወንድሞቻችን ማወቅ የሚኖርባቸው ሃቅ የ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ዘልቆ ያልገባቸው ይልቁንም ኢትዮጵያን ለማፍረስ "የአክሱም ሃውልት ለወላይታ ምኑ ነው" ሲሉን የነበሩት መለስ ዜናዊና ጄሌዎቹ ከስልጣን እስካልወረዱ ድረስ መልካም እቅዶች ሁሉ የተስፋ እንጀራዎች ከመሆን የዘለሉ አለመሆናቸውን ነው። ስለዚህ አገራችንን ከገባችበት አዘቅት ውስጥ ለማውጣትና እርስ በርሳችን በዘር ተከፋፍለን እንድንተላለቅ መለስ ዜናዊ ካዘጋጀልን ወጥመድ ለማምለጥ ከሁሉም አስቀድመን የርሱን ዘረኛ አገዛዝ በተባበረ ትግል ለመጣል በህብረት መነሳት ይኖርብናል። ይህ አባይን በአስተማማኝነት ለመገንባት የሚያስችለውንም ሃይል ይፈጥራል።

**ጆሮ ያለው ሁሉ ይስማ !!**
**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## በአዋሳ በርካታ ታዋቂ ባለሃብቶች ታሰሩ

በአዋሳ ከተማ በተለያዩ የንግድ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ በርካታ ነጋዴዎች በዘረኛውና አምባገነኑ ባለስልጣናት ትእዛዝ ወደ እስር ቤት እየታጎሩ መሆኑን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዘገባ ገለጸ፣ ፣ ነጋዴዎቹ በገፍ ወደ ማጎሪያ እስር ቤት እየተላኩ ያሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት ) አልከፈላቺሁም በሚል ሽፋን እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት እነኝህ የነጋዴው ማህበረሰብ አካል የሆኑት የአዋሳ ከተማ ነዋሪዎች ወደ እስር ቤት እንዲታጎሩ ምክንያት ነው የተባለውን የቫት ክፍያ በወቅቱ ከፍለው ያጠናቀቁ መሆናቸውን ነገር ግን ክፍያውን መክፈላቸውን በመግለጽና በማብራራት ለምን እንታሰራለን ብለው ቢጠይቁም ሰሚ ሊያገኙ ያልቻሉ መሆኑ ታውቋል።

ታሳሪ ነጋዴዎች ከሆኑት ውስጥ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለገ የአንደኛው ነጋዴ ወንድም መሆኑን የገለጸ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ያነጋገርው ግለሰብ እንደገለጸው፣ ወንድሙን የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት ወደ እስር ቤት የወሰዱት በቫት ክፍያ አለመከፈል ሳይሆን፣ በከተማው ዉስጥ እየተባባሰ በመጣው ጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ አገዛዙን አይደግፉም የሚባሉት ሁሉ ሊነሳ ይችላል ተብሎ ለሚፈራው ህዝባዊ አመጽ ሃይል እንዳይሆኑ በፍርሃት ለማሸማቀቅ ታስቦ እንደሆነ ገልጿል። በመቀጠልም፣ ዘረኛው አገዛዝ ዜጎችን ለማፈን በግፍ ወደ እስር ቤት ማጎሩን ቢቀጥልም፣ ከፍተኛ ብሶት ያለበት ህዝብ ስሜቱን መቆጣጠር ከማይችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰና ነጻነቱንም በትግሉ ለመቀዳጀት እየሰራ ነው ብሏል።

ዘረኛው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ባለስልጣናት፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኦነግ አባል ናቺሁ በማለት በፓርላማ ምክር ቤት ለረጂም ጊዜ ሲሳተፉ የነበሩ የመድረክ አባላትን፣ ህዝባዊ አመጽ ለማነሳሳት ትቀሰቅሳላቺሁ በማለት በርካታ የሆኑ ወጣቶችን፣ እንዲሁም የተለያዩና ፍጹም ከባለጉዳዩቹ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን ውንጀላዎች በመፈብረክ በርካታ ዜጎችን ወደ እስር ቤት እየወረወሩ እንደሆነ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ አይዘነጋም፣ ፣ ከዚህም በተጨማሪ የዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ የአንድነት ፓርቲ አባላትን ህዝባዊ አመጽ እንዲነሳ እየሰሩ ለመሆኑ መረጃዎች አሉን እናም ርምጃ እንወስድባቺሁአለን በማለት በምክር ቤት ተብየ ስብሰባ ላይ መዛቱ አይዘነጋም።

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ለ4ኛ ጊዜ የተከራየው ሳታላይት ጃም ተደረገ

በዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ተደጋጋሚ አፈና እየተካሄደበት ያለው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ኢሳት ለ4ኛ ጊዜ የሳታላይት ጣቢያ ለመቀየር የተገደደ ቢሆንም በአዲሱ የሳታላይት በአዲሱ ሳታላይት ላይ የተጀመረው ስርጭት ከአንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ከፍተኛ ጉልበት ባለው የሳታላይት ሞገድ መጥለፊያ መመታቱን ኢሳት አስታወቀ።

የመለስ ዜናዊ አፋኝ አገዛዝ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ለመገደብ በሚያካሁደው አምባገነናዊ እርምጃ በአገር ውስጥ የሚታተሙት ነጻ ጋዜጦችን ፍቃድ በመከልከል፤ ፍቃድ ያገኙትን ደግሞ በማስፈራራት፤ በማወከና የህትመት ዋጋ በመጨመር መንቀሳቀስ እንዳይችሉ እያደረገ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከአገር ውጪ ወደ ኢትዮጵያና አካባቢው በሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚደረጉ ስርጭቶችን በሙሉ ለማፈን ከፍተኛ የሆነ የአገሪቱን ሃብት እያፈሰሰ እንደሚገኝ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ሳይቀር ስለሰብዓዊ መብት አያያዝ ይፋ በሚያደርግበት አመታዊ ሪፖርቱ ገልጾአል።

ህዝባችን ምንም አይነት ነጻ የሆነ መረጃ እንዳያገኝ እና ከወያኔ የዜና ማሰራጫዎች የሚተላለፉትን የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ብቻ እየተጋተ እንዲኖር ለማድረግ ከደሃው ህዝባችን ጉሮሮ በተነጠቀ ገንዘብ ነጻና ገለልተኛ የሆነ መረጃ የሚያስተላልፉትን መገናኛ ብዙሃን የሚያፍን መሳሪያ በውድ ዋጋ ከቻይና እየተገዛ አገልግሎት ላይ መዋል በጀመረበት በዚህን ሰዓት ቁጥሩ ከ3 ሚሊዮን በላይ የሆነው የአገሪቱ ዜጋ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ተገልጾ በአገዛዙ በኩል ለውጪ መንግስታት የልመና ጥሪ ቀርቦአል። ወያኔ በአገሪቱ ውስጥ አስፍኛለሁ ስለሚለው እና በየዕለቱ ዜጎችን የሚያደንቁርባቸው ፍትህ፤ እኩልነት፤ ልማት እና እድገት እውነት በምድራችን ላይ የሚታዩ ቢሆን ኖሮ የሌሎች መገናኛ ብዙሃን መኖር እነመለስ ዜናዊን ይህንን ያህል ሊያስፈራ የሚችልበት ወይም ለልማት እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ሊውል ይችል የነበረ ብዙ ሚሊዮን ብር ወጪ እየተደረገ በቀን አንድ ሰዓት ብቻ ከሚተላለፈው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ እስከ በሳምንት 2 ቀን ብቻ የሚተላለፈው የኢህአፓ ሬዲዮ ለመጥለፍ ባላስፈለገ ነበር የሚሉ ብርካታ ኢትዮጵያዊያን ናቸው።

ኢሳት ስርጭቱን ወደ አገር ቤት ከጀመረበት ቀን አንስቶ የወያኔ አፈና ለአንድም ቀን እንዳልተለየው የሚናገረው የኢሳት መስራች ቦርድ፤ ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ፍሬ እስኪያፈራና በአገራችን ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት እስኪረጋገጥ ድርስ ኢሳትን በገንዘብ ወይም በሞገድ ጠለፋ ለማዳከም ወያኔ የሚያደረገውን ማናቸውንም አይነት መሰናክሎች ተቋቁሞ ለኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ለማገልገል የሚያስችለውን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት በፈረንጆች አቆጣጠር ከአፕሪል 14 ቀን 2011 ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ እና አካባቢዋ ስርጭት እያደረገበት ያለው አዲሱ ሳታላይት አፕስታር (APSTAR) 2 አር በመባል የሚታወቅ እንደሆነና ይህ ጣቢያ ቀደም ሲል ስርጭቱ ይተላለፍበት ከነበረው ታይኮም 5 አጠገብ የሚገኝ ሆኖ በ ሲ ባንድ 76.5 ድግሪ ኢስት ሆርዞንታል፣ ፍርኩዌንሲ 3840 ሜጋ ሄርዝ፣ ሲምቦል ሬት 27500 መሆኑን ን ከኢሳት የተሰጠ መግለጫ ያስረዳል። ኢሳት በውጪ የሚገኝ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገር ቤት ላለ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ይህንን አዲሱን ሳታላይት ፍሪኩዌንስ በማሰራጨት እንድትተባበር ጥያቄ አቅርቦአል።

የወያኔን አፈና ለመቋቋም ተብሎ በ8 የተለያዩ አጫጭር እና መካከለኛ ሞገዶች በሳምንት 3 ቀናት ጠዋትና ማታ ወደ አገራችን ስርጭት የሚያደርገውን የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮን ጨምሮ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ፤ የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ |ዶቼ ቬሌ| ፤ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሬዲዮ እና የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ሬዲዮም እንዲሁ እጂግ በጣም ብዙ ሚሊዮን ዶላር ወጪ እየተደረገ ከፍተኛ የሆነ የሞገድ ጠለፋ እየተካሄደባቸው በአገር ውስጥ የመሰማት ችሎታቸው ክፉኛ የተጎዳ መሆኑ ታውቋል።

## ከአባይ ግንባታ በፊት የታፈነው ህዝብ ይፈታ!! የሚል ወረቀት በአርባምንጭ ከተማ ተበተነ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወያኔ አፈና ሥርዓት ላይ ትዕግሥቱ መሟጠጡን በተለያየ ህዝባዊ ተቃውሞ እየገለጸ ካለው የደቡብ የአገራችን ክፍል በጋሞጎፋ ዋና ከተማ በአርባ ምንጭ ህዝቡን ለተቃውሞ የሚቀሰቅሱ ጽሁፎች መበተናቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአርባ ምንጭ አስታወቀ።

በተበተኑት ወረቀቶች ላይ ከታዩት መፈክሮችና ቀስቃሽ መልዕክቶች ከፊሎቹ “ ከአባይ ግድብ በፊት የታፈነው ህዝብ ይፈታ! ከውትድርና ቅጥር በፊት በሱማሌ፤ በቡሩንድ በዳርፉር የተገደሉ ወገኖቻችን መርዶ ለዘመድ አዝማድ ይነገር! ባድሜን በህግ አሸንፈናል በማለት በሃሰት ሰላማዊ ሰልፍ እንዲንወጣ ያደረጉን ስዩም መስፍንና አጋሮቹ ለፍርድ ይቅረቡ!! በስውር የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር ይፋ ይውጣ !! አምባገነኖች አባይን አይገድቡም!! ከግድቡ በፊት ለተራቡት ዳቦ ይሰጥ !! የሚሉ ይገኙበታል።

በአርባምንጭ የሚገኙ የወያኔ ካድሬዎችና የዞኑ አስተዳዳሪዎች እየተባባሰ የመጣውን የህዝብ ስሜት እንዴት ለማረጋጋት እንደሚቻል ለመምከር አስቸኳይ ስብሰባ ጠርተው እንደነበርና በስብሰባው ወቅት በተደረገው ውይይት ካዲሬዎች ለሁለት በመከፈል ከፊሎቹ የህዝቡን ፍላጎት እና ጥቅም ማስጠበቅ ስላልቻልን ሥራ እንልቀቅ አሊያም ለህዝብ ጥያቄ ተገቢው ምላሽ ይሰጥ እስከማለት እንደደረሱ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ወያኔ የህዝባችንን ትኩረት ወደ አባይ ግድብ ግንባታ በማዞር በሰሜን አፍርካ የተነሳው አይነት ህዝባዊ ማዕበል በአገራችን እንዳይቀጣጠል ለማዘናጋት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የጀመረው ዘመቻ አርባምንጭን ጨምሮ በተለያየ የአገራችን ከተሞች እንዲሁም ባለፈው ቅዳሜ ሚያዚያ 1 እና 2 በሰሜን አመሪካ ሳይሳካ እንደቀረ ገሃድ ወጥቶአል።

## ህዝብ ሲያስመርር የነበረው የሐረሪ ክልል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

(ከገጽ 1 የዞረ)

አገዛዝ ከፍተኛ ውጥረትና ፍርሃት ስላለበት ህብረተሰቡን በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ አፍኖ እንደሚገኝ፣ በሰበብ አስባቡም ወደ እስር ቤት እየወሰደ እንደሚያጉር ገልጻዋል፣ ፣ በመቀጠልም ይህ አፈናና ጭቆና ለአገዛዙ ባለስልጣናት መፍትሄ መስሎ ይታያቸው እንጂ፣ ህዝብ ብሶትና ምሬት ሲበዛበት እንዲህ አይነት ርምጃ መውሰዱ አዲስ ነገር አይደለም፣ በዚህ የሚያቆምም አይደለም ብለዋል፣ ፣ በመጨረሻም ወያኔ በምንም መልኩ ይሁን ለህዝብ ጆሮ ሰጥቶና ችግራችንን ተገንዝቦ መፍትሄ ያመጣል የሚል ተስፋ ፍጹም የሌለን በመሆኑ፣ አገዛዙ እስኪወገድ ድረስ በየግላችን የምንችለውን አይነት የተናጠል ርምጃ መውሰዳችን ይቀጥላል በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

## የኢትዮጵያን ወቅታዊ ፖለቲካ አስመልክቶ የኦሮሞ ወጣቶች . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

(ከገጽ 2 የዞረ)

5. ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነዉ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ህይወት የተመሰረተዉ በግብርና ላይ ሲሆን በ1960ዎቹና በ70ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተነሳዉና በ1974 አብዮት እልባት ያገኘዉ የመሬት ላራሹ ጥያቄ የንጉስ ሃይለ ስላሴን አገዛዝ ከስልጣን ያስወገደ፡ ሕዝብን በፖለቲካ ዙሪያ ያስተበበረ እንደነበር ይታወሳል። ይሁን እንጂ የሕወሃት አገዛዝ ዳግመኛ ወደ ነበርንበት ለመመለስ የሚከተለዉ መሬትን በገፍ ለዉጭ ባለሃብቶች የመስጠት ፖሊሲ ሕዝባችንን ከመሬቱ የሚያፈናቅለዉ፡ ባለቤትነት የሚያሳጣዉ፡ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሚያገልለዉ፡ ስራ አጥነት የሚያስከትልና ዘመናዊ ባርነት ዉስጥ የሚጥል በመሆኑ፡ **ይህ ፖሊሲ ባስቸኳይ እንዲቆምና እስከዛሬ የተደረጉት አለም አቀፍ ስምምነቶች ዋጋ እንደሌላቸዉ ተቆጥረዉ እንዲሰረዙ**
6. ኢትዮጵያ ባለፉት 20 አመታት እጅግ አስከፊ ወደ ሆነ ሁኔታ ዉስጥ በመግባት ላይ የምትገኝ ሲሆን በህግ አዉጪዉ፡ በሕግ አስተርጓሚዉና በህግ አስፈፃሚዉ መካከል ምንም አይነት የስልጣን ክፍፍል የማይታይበት፡ በስታሊናዊ መንግስት እንደሚታየዉ ሁሉ **ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ በህዝብ ሳይመረጡ እራሳቸዉ በፈጠሩት መዋቅር አማካይነት ስልጣኑን ሁሉ በብቸኝነት የሚቆጣጠሩ በመሆኑ ስልጣናቸዉን በአስቸኳይ እንዲለቁ**
7. ከ90 የማያንሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በህግ ተመዝግበዉ በሚንቀሳቀሱበት አገር ባለፈዉ ግንቦት 2010 በ99.6 በመቶ ድምፅ ህወሃት/ ኢህአዴግ አሸነፍኩ የሚለዉ ምርጫ ተቀባይነት የሌለዉ፡ የምርጫ ቦርዱ የመንግስት ሌላ እጅ በመሆኑ፡ የአገሪቱ ሀብትና ንብረት፡ የመገናኛ ብዙሃን፡ የፌዴራል ፖሊስና የፀጥታ ሃይሎች የገዢዉ ፓርቲ መሳሪያ በሆኑበት የተካሄደ፡ በዚህ ምክንያት **ምርጫዉ የተጭበረበረና አሳፋሪ በመሆኑ ሁለቱም ምክር ቤቶች በአስቸኳይ እንዲበተኑ፡ ከሁሉም የነፃነት ንቅናቄዎችና ለማህበራዊ ፍትህና ለዲሞክራሲ የቆሙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳታፊ የሚሆኑበት የሽግግር መንግስት እንዲመሰረት** ብሄራዊ የኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ-ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ባወጣ የአቋም መግለጫ ጠይቋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org